# <u>እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2019 የነበረው</u>
# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>


በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሁለተኛዉ አሥር ቀናት የወቅቱ ዝናብ ሰጪ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በይበልጥ የሚጠናከሩበትና የዝናቡ ስርጭትም አብዛኛዉ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን የሚያዳርስ ሲሆን፤ በመጠንም ረገድ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ የሚመዘገብበት ጊዜ ነዉ፡፡ በዚህም መሠረት ባለፉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጪ የሆኑት የአየር ሁኔታ ገጽታዎች እየተጠናከሩ በመምጣታቸው የወቅቱ ዝናብ አብዛኛዎቹን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳረሰ ከመሆኑም በላይ በዚህ ጊዜ ደረቅ ሆነው በሚቆዩት በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ ቆላማ ሥፍራዎች ላይም አነስተኛ ዝናብ እንዲኖር አድርገዋል። የወቅቱ ዝናብ በቦታ ሥርጭት ከነበረው መስፋፋት በተጨማሪ በመጠን ረገድ አልፎ አልፎ ከበድ ያለ በመሆኑ በተለይ በመካከለኛው ኢትዮጵያ አንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የጎርፍ ክስተት እንዲኖር መንስኤ ሆነዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት በአሥሩ ቀናት አብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት የቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የትግራይ፣ የጋምቤላና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልሎች የተስፋፋ የክረምት ዝናብ አግኝተዋል። በተጨማሪም ምንም እንኳን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት በሀገሪቱ ምዕራባዊ አጋማሽ ላይ የተጠናከረ ቢሆንም፤ በሰሜን ምሥራቅ ቆላማ ቦታዎችና በምሥራቅ ኢትዮጵያ እንዲሁም በዚህ ወቅት ዝናብ በማይጠበቅባቸው የሀገሪቱ ደቡባዊው ክፍሎች ላይ ቀስ በቀስ የክረምቱ ዝናብ ተስፋፍቶባቸው ነበር። በሌላ በኩል ባለፉት አሥር ቀናት አብዛኛዎቹን የሀገሪቱ አካባቢዎች የሸፈነው ዝናብ በአንድ በኩል የክረምቱ ዝናብ መደበኛውን ፈር የተከተለ መሆኑን የሚያሣይ ሲሆን፤ በአንጻሩ ግን አልፎ አልፎ ነጎድጓድ ያዘለ ከባድ ዝናብ በተለያዩ ቦታዎች ላይ መከሰቱን ከዝናብ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል። ባለፉት አስር ቀናት ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል ለመጠቀስ ያህል በአለም ከተማ 35.3፣ በአይራ 37.5 በአርጆ 36.2 እና 41.2፣ በአይከል 30.1፣ በአደት 30.6፣ በአይሻ 49.4፣ በባህር ዳር 31.3፣ በባቲ 33.5፣ በቤጊ 33.6፣ በጨፋ 33.1፣ በደብረብርሀን 38.6 እና 43.1፣ በደብረታቦር 41.1፣ በድሬዳዋ 32.2፣ በእነዋሪ 32.2፣ በፍቼ 59.6 እና 31.8፣ በጋቲራ 43.2፣ በጊዮን 47.6፣ በጊምቢ 67.3፣ በጎሬ 39.2፣ በጅማ 56፣ በካችሴ 36.9፣ በምሀልሜዳ 41.2፣ በማጀቴ 30.5 እና 50.2፣ በማሻ 54.0፣ በመቀሌ 49.2፣ በሞጣ 47.7፣ በመካነሰላም 31.7 እና 74.5፣ በማይፀምሪ 43.0፣ 32.2 እና 90.4፣ በነጆ 50.0፣ በኑራኢራ 39.4 እና 47.6፣ በሾላ ገበያ 36.7፣ በሽሬ 46.1፣ በሻውራ 40.3፣ በሽራሮ 38.4 እና 56.0፣ በሲርባአባያ 40.5፣ በወረኢሉ 33.4፣ በወሊሶ 31.8፣ በነብለት 44.7 እና 41.0፣ በጎሎልቻ 44.6፣ በቡሬ 55.8 እንዲሁም በሳምሪ 42.5 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ ዝናብ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ሊመዘገብ ችሏል።


በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ ዝናብ ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በትግራይ ዞኖች፤ በአማራ፤ በሁሉም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፤ በጋምቤላ፤ ከባሌና ጥቂት የቦረና ዞኖች በስተቀር በሁሉም የኦሮሚያ ክልሎች፤ በአፋር ክልል ከዞን 01 በስተቀር፤ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ እንዲሁም በአዲስ አበባ፤ በድሬዳዋና ሀረሪ ከ5-232 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-8 ቀናት ያህል የዘነበ ሲሆን፤ ከአፋር ክልል በዞን 01 እና በጎዴ ከ5 ሚ.ሜ በታች የሆነ ዝናብ ከ2 ላነሱ ቀናት ያህል ዘንቧል (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አሥር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር በትግራይ፣ ከአማራ የሰሜን ጎንደርና ዋግህምራ እንዲሁም ከጥቂት የሰሜን ወሎ ክፍሎች በስተቀር በሁሉም የአማራ ክልሎች፤ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች የአሶሳና የከማሺ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ የምዕራብ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጅማ፣ ሀሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ ሀረርጌ፣ አርሲና ቦረና ዞኖች፣ የጋምቤላ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋና የቤንች ማጂ ሰሜናዊው ክፍል፤ አብዛኛዉ የአፋር ክልል ዞኖች እንዲሁም አዲስ አበባና ድሬዳዋ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ ቀናት



ካርታ 3    እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20 /2019 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር







ከመደበኛ በታች    መደበኛ    ከመደበኛ በላይ

# እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁላይ ሁለተኛዉ አሥር ቀናት የተገኘዉ እርጥበት በአብዛኛዉ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አከባቢዎችን ያዳረሰ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አብዛኛው መኸር አብቃይ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ጥሩ የአፈር እርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ እየተካሄደ ለነበረው የመኸር እርሻ እንቅስቃሴ፣ የማሳ ዝግጅትና የዘር መዝራት ስራዎችን በጊዜ ለማከናወን አመቺ ሁኔታ የነበረዉ ሲሆን፤ አስቀድመው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የረጅም ጊዜ ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር የጎላ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ምንም እንኳን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት በሀገሪቱ ምዕራባዊ አጋማሽ ላይ የተጠናከረ ቢሆንም፤ በሰሜን ምሥራቅ ቆላማ ቦታዎችና በምሥራቅ ኢትዮጵያ እንዲሁም በዚህ ወቅት ዝናብ በማይጠበቅባቸው የሀገሪቱ ደቡባዊው ክፍሎች ላይ የነበረው መጠነኛ እርጥበት በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አወንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ በተለይም በመካከለኛው ኢትዮጵያ አንዳንድ ሥፍራዎች የነበረው ከባድ ዝናብ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ለጎርፍ መከሰት ምክንያት በመሆን በግብርናው ሥራ ላይ በጥቂቱ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2019 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




## እ.ኤ.አ ከጁላይ 11-20/2019 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 11-20 ጁላይ 2019 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በሀገሪቱ ምዕራባዊ አጋማሽ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የተስተዋለ ሲሆን፤ ከዚህ ጋር ተያይዞ አብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ ባሮአኮቦ፣ የመካከለኛውና የላይኛው ኦሞጊቤ እና አዋሽ፣ የላይኛው ስምጥ ሸለቆ እና አፋርደናከል፣ ጥቂት የላይኛዉ ገናሌ ዳዋ እንዲሁም የዋቢሸበሌ ተፋሰሶች ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል አብዛኛው ዋቢሸበሌ፣ ኦጋዴን እና ገናሌዳዋ፣ ምስራቃዊ አፋር ደናከል፣ የታችኛው አዋሽ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥሸለቆ እንዲሁም የታችኛው ኦሞጊቤ ተፋሰሶች በአብዛኛው ከክፊል ደረቅ እስከ ደረቅ ሁኔታ የተስተዋለባቸው ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ በመሆኑም ባለፉት አስር ቀናት የተገኘው እርጥበት ለውሃ ፍላጎት ግብዓት አስተዋፆ ከማድረጉም በላይ በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ በተከታታይ ከባድ ዝናብ በመኖሩ የወንዞች ሙላት እና በረባዳ ቦታዎች ላይ ውሃ መተኛት ተከስቷል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2019 ድረስ በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

ባለፉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ተጠናክረው በመቆየታቸው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ ቦታዎች ላይ የተሰፋፋ ዝናብ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ። በተመሳሳይ መልኩም በሚቀጥሉት አሥራ አንድ ቀናት በተለያዩ ሀገሪቱ ሥፍራዎች ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረውና ከዚሁም ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምእራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ የአርሲና ባሌ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አገው አዊ፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን ሸዋ፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ዞኖች፤ ሁሉም የትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ደግሞ ዞን 1 ፣ 3፣ 4 እና ዞን 5፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋና የቤንች ማጂ፣ የጉራጌ፣ የሀዲያ፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋና የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበና አልፎ አልፎም በአንዳንድ ቦታዎችም ላይ ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በከባድ ዝናብ ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊከሰት ይችላል። ከዚህም ሌላ ከሶማሌ ክልል ደጋሃቡር፣ ጅግጅጋ እና ሲቲ፣ ድሬዳዋ እና ሀረሪ እንዲሁም ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የሰገን ህዝቦች በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ቦታዎች በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ።

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ስራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ከላይ በተሰጠው ትንበያ መሠረት በሚቀጥሉት የጁላይ ሶስተኛዉ አሥራ አንድ ቀናት በተለያዩ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረውና ከዚሁም ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ጥሩ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸውና በተለይም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ይበልጥ የተጠናከረ ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ ለግብርናው ስራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረዉና አስቀድመው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የሚገኘዉ እርጥበት በጎ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የመኸር ወቅት እርሻ እንቅስቃሴን ዘግይተው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የአፈር

ውስጥ እርጥበትን እንደሚያሻሽልና የመኸር ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የዉሃ ፍላጎት መሟላት እና በአሁኑ ጊዜ እርጥበት በማግኘት ላይ ለሚገኙት በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽና የመጠጥ ዉሃ አቅርቦትን ለማሻሻል የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል። በሌላ በኩል በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ስለሚችል በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማንጣፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላም በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት በተለይም በተከታታይ ዝናብ እያገኙ ባሉ ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸው ቦታዎች አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ አካባቢዎች ከእርጥበት መብዛትና አልፎ አልፎ በየጣልቃው ከሚኖረው ሙቀት ጋር የአረምና የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት ሊኖር ስለሚችል የሚመለከተው ክፍል በየጊዜው የማሳ ጉብኝት በማድረግ ጥንቃቄ እንዲወስድ እንመክራለን፡፡

## <u>እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2019 የሚኖረው የአየር ሁኔታ</u>
## <u>አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

የክረምቱ ዝናብ በሚቀጥሉት አስራ አንድ ቀናት ውስጥ በተጠናከረ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በሚያገኙት ተፋሰሶች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረው ትንበያው ያመለክታል። ይህንን ተከትሎ በአብዛኛዉ የተከዜ፣ □ኦሞጊቤ፣ የአባይ፣ የላይኛውና መካከለኛው አዋሽ፣ ስምጥሸለቆ አፋር ደናከል ተፋሰሶች እንዲሁም የባሮአኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በሌላ በኩል የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛዉ ኦጋዴን እንዲሁም የታችኛዉ አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከእርጥበታማ እሰከ መጠነኛ እርጥበት ሊኖራቸው እንደሚችል ይጠበቃል። የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ላይ እንደሚቆዩ ይጠበቃል። በተጨማሪም በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል ትንበያው ይጠቁማል። ይህንን ተከትሎ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ቦታዎች ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊከሰት ስለሚችል ክትትልና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።